Inova™

Inova Fairfax Medical Campus

# ታካሚዎች መረጃ መመርያ

## ስልክ ቁጥር

### አስፈላጊ ቁጥሮች

- **ነርስ መሪዎች:** እርስዎን ለማገልገል 24/7 ዝግጁ ናቸው፡፡ እባክዎትን የነርስ መሪዎች ስምና ስልክ ቁጥር በካርድ ቦርዶ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡
- **የፀሎት ስፍራ: 703.776.3767**
- **የጠፋና የተገኘ: 703.776.2280**
- **ታካሚዎች ግንኙነት/ታካሚዎች ተጣባቂዎች: 703.776.3663**

### ታካሚ ስልክ

የእርስዎ ስልክ ቁጥር በእንክብካቤ ቦርድ ላይ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ ወደ እርስዎ የሚደወሉት ስልኮችን ከ 7 ኤኤም እስከ 10 ፒኤም ማንሳት ይችላሉ፡፡ በማንኛውም ሰዓት **9** በመጫን ከዛም የአካባቢውን ኮድ ያስገቡ በመቀጠልም የሚፈልጉት ስልክ ቁጥር በማስገባት ይደውሉ፡፡

## አገልግሎቶች

### ምግብና መጠጦች

- **ሳውዝ ሳይድ ካፌ:** ሁሌ ከ5:30 ኤኤም – 10 ፒኤም ክፍት ሲሆን በ ሳውዝ ታካሚዎች ህንፃ የመጀመርያ ፎቅ ላይ ይገኛል፣ ሳውዝ ሳይድ ካፌ ሳንዱችና ሌሎች ቀለል ያሉ ምግቦችን ያቀርባል (ግሪል ከ 5:30 – 6:30 ኤኤም ብቻ)፡፡
- **ሀርት ሄልዝ ካፌ:** ከሰኞ እስ ዓርብ 7 ኤኤም - 2 ፒኤም፡፡ በ Inova Schar Heart and Vascular ከልብና ቫስኩላር ሎቢ በላይ ሁለተኛ ፎቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ሀርት ሄልዚ ካፌ ሳንዱችና ሌሎች ቀለል ያሉ ምግቦችን ያቀርባል፡፡
- **ፓርክ አቨኒው ካፌ:** ከሰኞ እስ ዓርብ 6:30 ኤኤም - 5 ፒኤም፡፡ በአትሪም የመጀመርያ ፎቅ ላይ ይገኛል፤ ፓርክ አቨኒው ካፌ የተለያዩ የቁርስና ምሳ አገልግሎት ምግቦች ያቀርባል፡፡

### መዝናኛ

**ነፃ Wi-Fi ለማግኘት:**

- በ ‹‹ቅንብር›› ውስጥ Wi-Fi የሚለውን ይምረጡ
- ‹‹ኔትዎርክ ምረጥ›› የሚለውን ይምረጡ
- ‹‹IHSPublic›› ይምረጡ
- ‹‹በሕጉ እስማማለሁ›› የሚለውን ይጫኑ

## ሌሎች አገልግሎቶች

**ATM:** ATM በ Inova Schar Heart and Vascular እንዲሁም ደቡብ የታካሚዎች ህንፃ መሀከል በሚያገናኘው የመጀመርያ ፎቅ፣ በ Inova L.J. Murphy Children's Hospital/Inova Women's Hospital እንግዳ መቀበየ በደቡብ በኩል ያለው ካፍቴርያ እንዲሁም በ Inova Schar Heart and Vascular የስጦታ መሸጫ ውስጥ ይገኛል፡፡

## ጠያቂዎች ፖሊሲ

በቅርቡ የወጣውን የጠያቂዎች መመርያ ይመልከቱ:
**Inova.org/Visit**

ታካሚዎች ላያ ያተኮረ፣ ታካሚዎች ዋስትና ባለው፣ ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ፀጥታና እንክብካቤ ባለው አካባቢ እንዲያገግሙ ማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡

ጠያቂዎችም በተገቢው የክሊኒካል መሪዎች ወይ በታካሚው በሚገልፀው ፍላጎት መሰረት ማሻሻያ ይደረግበታል፡፡ ድንገተኛ ችግሮች (ኢንፍሊወንዛ ወይ ሌላ ተላላፊ ሁኔታዎች) ከተከሰቱ የበሽታ መስፋፋት ደረጃን መቀነስ ላይ እንዲረዳ በጠያቂዎች ላይ ጊዝያዊ ገደቦች ሊጣሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ገደቦች ያለውን ሁኔታ መሰረት በማድረግ በአጠቃላይ ስርዓት፣ ሆስፒታሎች ወይ በተጠቁ የነርሲንግ ክፍሎች ላይ የሚተገበር ሊሆን ይችላል፡፡

**የስጦታ መሻጫ ሱቅ:** በጊቢው ውስጥ ሶስት የስጦታ መሸጫ ሱቆች አሉ፡፡

- ታካሚዎች ህንፃ: **703.776.3470**
- Inova Schar Heart and Vascular: **703.776.7066**
- Inova የሴቶች/Inova የህፃናት: **703.776.6066**

**ኖታሪ አገልግሎት:** ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ8:30 ኤኤም - 3:30 ፒኤም በ**703.776.3663** በመደወል ያገኛሉ፡፡

## መውጣት

ከሆስፒታሉ እንዲወጡ ለመርዳት የእንክብካቤ ቡድኖ በጋራ የሚሰሩ ይሆናሉ:

- ሀኪምና/ሆስፒታሊስት የሚወጡበትን ቀን በመወሰን ትእዛዙን ይፅፋሉ
- የጉዳይ አስተዳደር ቡድን አባላት አገልግሎት ማቀናጀትና በተገቢ መልኩ ለመውጣት የሚያስፈልጎት ነገር ሁሉ እንዳገኙ ለማረጋገጥ ድጋፍ ያደርጋሉ
- ነርስዎ ሲወጡ ስለሚኖረው መመርያ ከእርስዎ ጋር ይገመግማሉ
- ለመውጣት ዝግጁ ከሆኑና ነገር ግን መድሀኒት እንዲሞላሎት ወይ ወደ ቤት የሚወስዶት ማጓጓዣ እየጠበቁ ከሆነ፤ ተንከባካቢዎ ወደ ሆስፒታል ስዊት በማምጣት ከእኛ የሚኖሮትን ቆይታ እዛ ላይ ያጠናቅቃሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **Inova.org/IFMCDischarge** ይጎብኙ፡፡

## የግል ንብረቶች

Inova Fairfax Medical Campus ሞባይል ስልክ፣ መነፅር፣ ዴንቸር፣ ማዳመጫዎችና ሌሎች ንብረቶችን ጨምሮ ለሚጠፋ ማንኛውም የግል ንብረት ተጠያቂ አይደለም፡፡ እባክዎትን ከክፍሉ ከመውጣቶ በፊት ሁሉም ውድና የግል ንብረቶን መያዞትን ያረጋግጡ፡፡ የጠፋቦት ወይ ያገኙት ንብረት ካለ ሪፖርት ለማድረግ የእንክብካቤ ቡድን አባላትን በ**703.776.2280** ያግኙ፡፡

## የእንክብካቤ ቡድኖ

**ሆስፒታሊስቶች፣ ሀኪሞችና ሌላ እንክብካቤ አቅራቢዎች:** ሆስፒታሊስት ማለት በሆስፒታል ውስጥ የሚገኙ ታካሚዎችን መንከባከብ ላይ ስፔሻላይዝድ ያደረገ ሀኪም ነው፡፡ ሆስፒታሊስት፣ ስፔሻሊቲ ሀኪምና አድቫንስድ ፕራክትሽነር ማለትም እንደ ነርስ ፕራክትሽነር፣ አዋላጅና የሀኪም ረዳቶች የመሳሰሉት ባለሙያዎች በሆስፒታል በሚቆዩበት ግዜ እንክብካቤ ያደርጋሉ፡፡

**ነርሶች:** ነርሶች በሂደት ላይ ያለ እንክብካቤና ህክምና ያስተባብራሉ፣ ታካሚዎችን ደህንነትና ምቾት መጠበቅና ታካሚዎች ስለሚኖራቸው የእንክብካቤ እቅድ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡

**ክሊኒካል ቴክኒኮች፣ የህክምና ድጋፍና ፌልቦቶሚስት:** እነዚህ ባለሙያዎች የእንክብካቤ ቡድኑን በተለያዩ የታካሚዎች ፍላጎቶች ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

**ቴክኒሻንና ቴክኖሎጂስቶች:** እነዚህ ባለሙያዎች እንደ ኢሜጂንግ ላብራቶሪ የመሳሰሉትን ምርመራዎች ማካሄድ ላይ ስፔሻላይዝ ያደርጋሉ፡፡

**ተኝቶ ታካሚዎች አካላዊ መድህኒትና የማገገም ቴራፒስት:** ክሊኒካዊ ቴራፒስት ታካሚዎች እንቅስቃሴያቸው እንዲመለስ፣ ህመም ማነጅ ለማድረግና እንደ መብላት መልበስ የመሳሰሉ ክህሎቶችን እንዲቀጥሉ ይረዳል፡፡

**የአተነፋፈስ ቴራፒስት:** እነዚህ ቴራፒስቶች ከፍተኛ የሆነ የአተነፋፈስ ህክምና ከሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች ጋር በጋራ ይሰራሉ፡፡

## ጠቃሚ ምንጮች

**ፈጣን ምላሽ:** ሆስፒታል ሰራተኞች፣ ታካሚዎች ወይ ጠያቂዎች ድንገተኛ እደጋ ምላሽ ለማግኘት ከማንኛውም የሆስፒታል ስልክ በ **5555** መደወል ይችላሉ፡፡

**ቋንቋ አገልግሎት:** ከኢንግሊዝኛ ውጪ በሌላ ቋንቃ መጠቀም ለሚፈልጉ ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው ያለ ምንም ክፍያ የሰለጠኑ አስተርጓሚዎች አሉ፡፡

**የአካል ጉዳት መብቶች:** Inova Fairfax Medical Campus አካል ጉዳት ያለባቸው አሜርካውያን ሕግ እንዲሁም አካል ጉዳት ያለባቸው ቨርጂንያውያን ሕግ ዓላማዎችን ለማሳካት እንጥራለን፡፡ ፖሊሲውን በተመለከተ ጥያቄ ካሎት በ**703.776.3663** የታካሚውን ግንኙነት ቡድን ጋር ይደውሉ፡፡

**አስቀድሞ የሚሰጥ መመርያ:** እርስዎ ጥያቄ ካቀረቡ በራሪ ወረቀት ይቀርባል፡፡ እባክዎትን ዝርዝር ለማግኘት ነርስን ይጠይቁ፡፡

**መስማት የተሳነው/መስማት የሚቸገር:** መስማት የተሳናቸው ወይ መስማት የሚቸገሩ ታካሚዎችና ከቤተሰብ አባሎቻቸው ጋር ለመግባባት ያለ ምንም ክፍያ አክዝለሪ ኤድና የምልክት ቋንቋ አገልግሎት ያቀርባል፡፡

**ስነ ምግባር ማማከር:** የሆስፒታል ስነ ምግባር አማካሪ ቡድን ታካሚዎች ወይ ቤተሰቦቻቸው ስለ ሂወትና ሞት እንዲሁም ስለ ሂወት ጥራት በተመለከተ የማማከር አገልግሎት ያቀርባል፡፡

**እንክብካቤ ሕግ ዲዛይን:** ታካሚው ወደ እቤት በሚወጣበት ወቅት ይህ ሰው ታካሚውን ይረዳል፡፡

**ድጋፍ እንዲሰጥ የተወከለ ሰው *(Designated Support Person (DSP))*:** ታካሚው በህክምና ውስጥ በሚሆንበት ግዜ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ የሚሰጥ ግለሰብ (ታካሚው የሚወክለው ወይ ሕጋዊ ውሳኔ ሰጪ) ነው፡፡ ይህ የአእምሮ ጤና ለውጥ ያላቸው ወይ ከዚህ በፊት አካላዊ ጉዳት እንዳለባቸው ተለይቶ በአሁኑ ሰዓት ድጋፍ ለሚያገኙ ታካሚዎች የሚመለከት ነው፡፡

**MyChart:** ይህ ኦንላይን የጤና አስተዳደር መሳርያ ታካሚዎችን ከግል የህክምና ማስረጃዎቻቸው ጋር እንዲገናኙና እንዲሁም በማንኛውም ሰዓትና ቦታ እንዲገናኙ ያስችላል፡፡ በ **Inova.org/MyChart** ይመዝገቡ ወይ ወደ **855.694.6682** ይደውሉ፡፡

## የታካሚ እርካታ ዳሰሳ

ከወጡ በኋላ በኢሜይል፣ ፓስታ ወይ ፅሁፍ መልእክት ዳሰሳ ሊደርሶት ይችላል፡፡ የእርስዎ አስተያየት አገልግሎታችንን ለማሻሻልና የተሻለ አፈፃፀም ያሳየንበት ቦታ እንድንለይ ዕድል ይሰጠናል፡፡

## መኪና ማቆምያ

በሰማያዊ፣ አረንጓዴና ግራጫ ጋራዦች ላይ መኪና ለማቆም በቀን $5 ነው፡፡ ጠያቂው በ30 ደቂቃ ውስጥ ከወጣ ይህ ክፍያ ይሰረዛል፡፡ በሆስፒታሉ የስጦታ መሸጫ ሱቅ ውስጥ 10-ጥየቃ ማከለፍያ በ$25 ማግኘት ይችላሉ፡፡

ለ Inova Surgery Center ታካሚዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ 5:30 ኤኤም እስከ 10 ፒኤም ባለው ሰዓት በቀዶ ጥገና ማእከል መግቢያው ላይ ተጨማሪ መኪና ማቆምያ ማግኘት ይቻላል፡፡ የተወሰነ የመንቀሳቀስ አቅም ያላቸው ታካሚዎች ወይ ጠያቂዎች ካሉ በዋናው መግብያ ማውረድ ይቻላል፡፡

## የህዝብ ማጓጓዣ

ለአውቶቡስ ወይ ታክሲ አገልግሎት ለማግኘት **Inova.org/IFMCTransportation** ይጎብኙ፡፡

## ፋይናንሳዊና ኢንሹራንስ መረጃ

ለክፍያ ጥያቄዎች፣ ወደ **571.423.5750** ይደውሉ፡፡

G39372AM/1-24